## የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ መንግስት
## የከተማ ፖሊስ ክፍል


# ታይትል ስድስት (Title VI ) አድልዎ የሚያስወግድ ፖሊሲ

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ በ1964 በወጣውና ታይትል ስድስት (Title VI) በመባል በሚታወቀው የሰብዓዊ መብቶች ህግ መሰረትና ከዚህ ጋር በተያያዙ አድልዎን በሚከለክሉ የተለያዩ ህጎች መሰረት፤ ማንም የመንግስት የገንዘብ እርዳታ የሚያገኝ ድርጅት፤ ማንም ሰው በዘሩ ምክንያት፣ በቆዳ ቀለሙ፣ በዜግነቱ፣ በጾታው፣ በዕድሜው፣ በስንክልናው፣ በገቢው መጠን፤ ወይም የእንግለዘኛ ቋንቋ ባለመቻሉ ምክንያት በላዩ ላይ አድልዎ እንዳይፈጸምበት ወይም በሆነ ነገር እንዳይካፈል ወይም የሚገባውን ጠቀሜታ እንዳያገኝ አለመታገዱን ወይም አለመከልከሉን  የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎብያ የፖሊስ ክፍል ያረጋግጣል።

ይሄው የከተማ የፖሊስ ክፍል (MPD)፤ የመንግስት እርዳታ የሚያገኚ ይሁኑ የማያገኙ ቢሆኑም፤ ባሉት ፕሮግራሞችና በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ በማንኛውም ሰው ላይ ምንም ዓይነት አድልዎ አለመደረጉን ያረጋግጣል።

በተጨማሪም፤ ኤም-ፒ-ዲ( MPD) ሌላ ተቋም የመንግስት የገንዘብ እርዳታ እንዲያገኝ  ካደረገ በኋላ፤  ተቋሙ በሚያደርገው ማንኛውም ስምምነት ላይ በዚህ ታይትል ስድስት ((Title VI) በተባለው ጸረ-አድልዎ በሆነው ህግ እንዲገዛ ማድረግ አለበት።

በታይትል ስድስት (Title VI) ህግ መገዛት ማለት ከመንግስት የገንዘብ እርዳታ የማግኘት ደረሰኝ እንደማግኘት ማለት ነው።ኤም-ፒ-ዲ (MPD) በዚህ የታትል ስድስት( Title VI) ፕሮግራም ማረጋገጫ ላይ  ፈርሞበታል።የታትል ስድስት (Title VI) ፕሮግራም አስተባባሪ፣ አልፎንሶ ሊ (Director Alphonso Lee) ይህ ታትል ስድስት (Title VI) የሚባለው ህግ በስ፤ በህጉ መሰረት በስራ እንዲተረጎም የማድረግ ሃላፊነትንና  ስልጣን ተቀብለዋል። ይህም ብቻ ሳይሆን በህግ 49 C.F.R. ክፍል 21 እና በ49 C.F.R. ክፍል 303 ህግ መሰረት የኢም-ፒ-ዲ (MPD) ሰራተኞች በሙሉ የታትል ስድስት (Title VI) ህግ ሃላፊ በትክክል በስራ እንዲተረጎም እንዲያደርጉ እገዛቸውን ይሰጧቸዋል።



መጋቢት (March) 8 ቀን 2023
ቀን

ሮበርት ጄ ኮንቴ  III (Robert J. Contee III)
የከተማ ፖሊስ ክፍል ሃላፊ
(Chief, Metropolitan Police Department)